በፌዴራል ጤና ሚኒስቴር
የኢትዮጵያ የሕብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት
ዜና ኢ.ሕ.ጤ.ኢ.

መጋቢት 2014 ቅጽ 5 ቁጥር 12

በኢ.ሕ.ጤ.ኢ. የህዝብ ግንኙነትና ኮሙኒኬሽን ቢሮ በየወሩ የሚዘጋጅ

በሀገራችን የጤና አትላስ ሰነድ ይፋ ሆነ

በሀገራችን የጤና ስርዓት ታሪክ ውስጥ ፋና ወጊ የሆነው የጤና አትላስ የመጀመሪያው ሰነድ በኢትዮጵያ የሕብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት አዘጋጅነት ተጠናቆ ለምርቃት መብቃቱ ተገለጸ።

በኢትዮጵያ የሕብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት ስር የሚገኘው ብሔራዊ የጤና መረጃ አስተዳደር ቅመራና ትንተና ማዕከል ከጤና ሚኒስቴር ጋር በመተባበር ባዘጋጀው ወርክሾፕ ላይ እንደተገለጸው በኢትዮጵያ የጤና ስርዓት ውስጥ የመጀመሪያ የሆነውን የጤና አትላስ (Health Atlas) ለምረቃ በቅቷል። ይህ የጤና አትላስ ኢትዮጵያ ውስጥ ከ 1990-2019 (እ.ኤ.አ.) በተለያዩ ክልሎች እና አካባቢዎች የተከሰቱ በሽታዎች እና የበሽታዎችን ስርጭት ለማሳየት ታስቦ የተዘጋጀ ነው፡ ፡ በመሆኑም የዚህ አትላስ ዋነኛ ተጠቃሚዎች የጤና ሚኒስቴር እና የክልል ጤና ቢሮዎች ሲሆኑ በተለያዩ ውሳኔዎች ወቅት መረጃ እና ምርምርን መሠረት ያደረገ ውሳኔን እንዲወስኑ እገዛ ያደርጋል ተብሎ ተስፋ ተጥሎበታል።

ዶ/ር ሩት ንጋቱ በጤና ሚኒስቴር የሚኒስትሩ ቺፍ ኦፍ ስታፍ ባደረጉት ንግግር እንዳስታወቁት በሀገራችን

. . .ወደ ገጽ 4 ዞሯል

የኮሌራ ክትባት ዘመቻ በአፋር እና አማራ ክልሎች ተካሄደ

የኢትዮጵያ ሕብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት ከአፋር ሕብረተሰብ ጤና እንዲሁም ከአማራ ክልል የሕብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩቶች ጋር በመተባበር በጦርነት ለተፈናቀሉ እድሜያቸው ከአንድ አመት በላይ ለሆኑ የሕብረተሰብ ክፍሎች በሙሉ የኮሌራ በሽታ መከላከያ ክትባት የመስጠት ዘመቻ አካሄደ።

የኢትዮጵያ የሕብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት ምክትል ዋና ዳይሬክተር አቶ አስቻለዉ አባይነህ ኢንስቲትዩቱ ከጤና ሚኒስቴር ፣ ከክልሎች እና ከአጋር አካላት ጋር በመተባበር በሃገራችን የተለያዩ ክፍሎች የሕብረተሰብ ጤና ስጋቶች ላይ የቁጥጥር እና ምላሽ ስራዎችን በመስራት ላይ እንደሚገኝ ገልፀዋል።

የኮሌራ በሽታ ወረርሽኝ በአገራችን ኢትዮጵያ በተደጋጋሚ ሲከሰት መቆየቱ የሚታወቅ ሲሆን ከ2008 ዓ.ም. ጀምሮ ወረርሽኙ በሁሉም ክልሎች መከሰቱ እና በተሰራዉ የመከላከልና የመቆጣጠር ስራዎች ወረርሽኙን በአብዛኛው ቦታዎች ላይ አላስፈላጊ ሞት እና ህመም ሳይከሰት መቆጣጠር መቻሉን ገልፀው፤ በቅርቡ በኦሮሚያ እና

. . .ወደ ገጽ 4 ዞሯል

የ2014 በጀት ዓመት ሁለተኛው የሕብረተሰብ ጤና አደጋ ቁጥጥር ፎረም ተደረገ

የኢትዮጵያ የሕብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት የ2014 በጀት ዓመት ሁለተኛው የሕብረተሰብ ጤና አደጋ ቁጥጥር ፎረም በተሳካ ሁኔታ በተቀመጠለት የጊዜ ሰሌዳ እና የውይይት ዕቅድ መሰረት በሐረር ከተማ የተካሄደ ሲሆን ቀጣዩም ፎረም በደቡብ ምዕራብ ክልል ይካሄዳል።

በፎረሙ ላይም የተለያዩ ተያያዥነት ያላቸው ሪፖርቶች የቀረቡ ሲሆን ባለፈው ፎረም ላይ እንዲተገበሩ በእቅድ ተቀምጠው የተፈጸሙ እና ያልተፈጸሙት ከነምክንያታቸው የቀረቡ ሲሆን ለቀጣይም እንዚህን ለመፈጸም ውይይት ተደርጎባቸው አቅጣጫ ተቀምጦላቸዋል።

የፎረሙን ውይይት የመሩት የኢትዮጵያ የሕብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት ም/ዋና ዳይሬክተር አቶ አስቻለው አባይነህ በውይይቱ ወቅት ለቀረቡ ሀሳቦች እና አስተያየቶች ምላሽ የሰጡ ሲሆን ከክልል ጀምሮ እስከ ፌደራል ድረስ በተቀናጀ መልኩ መሰራት እንዳለበት አስገንዝበዋል።

በዝግጅቱ መጨመረሻ ቀንም የፎረሙ ተሳታፊዎች በሐረር ከተማ የጽዳት ዘመቻ ያደረጉ ሲሆን በጁገል ሆሲፒታል የሚገኘውን የሕብረተሰብ ጤና አደጋዎች ማስተባበሪያ ማዕከልን ከጎበኙ በኋላ ቀጣይ ለሚያዘጋጀው ክልል እና ለሌሎች የክልል የሕብረተሰብ ጤና አደጋዎች ቁጥጥር ማዕከሎች የማስታወሻ ሽልማት ተሰጥቷል።

በሕብረተሰብ ጤና አደጋ ማስተባበርያ እና የክስተት አስተዳደር ስርዓት ዙሪያ ለሚመለከታቸው አካላት ስልጠና ተሰጠ

የኢትዮጵያ የሕብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት ከአጋር ድርጅቶች ጋር በመተባበር በሕብረተሰብ ጤና አደጋ ማስተባበርያ እና የክስተት አስተዳደር ስርዓት (IMS) ዙሪያ ለክልል ጤና ቢሮዎች/ጤና ኢንስቲትዩቶች፣ ለዞን ጤና መምሪያዎች፣ ለሀገር መከላከያ ጤና መምሪያ እና የፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን ጤና መምሪያ እንዲሁም ለጅማ ዩኒቨርሲቲ የአደጋ ማስተባበሪያ ማዕከል ባለሙያዎች ከመጋቢት 7 - 10/2014ዓ.ም በአዳማ ከተማ ስልጠና ሰጥቷል ።

ስልጠናው የሕብረተሰብ ጤና ድንገተኛ አደጋዎችን በፍጥነት ለመቆጣጠር በሕህብረተሰብ ጤና አደጋ ማስተባበርያ ማዕከል (Public Health Emergency Operation Center) እና የክስተት አስተዳደር ስርዓት (IMS) ላይ ግንዛቤን በማሳደግ የሕብረተሰብ ጤና አደጋ ባለሙያዎች መረጃን እና ሀብቶችን በብቃት እንዲያቀናጁ የሚያግዝ ነው።

የኢንስቲትዩቱ የስልጠና ማዕከል የ7ወር ሪፖርቱን አቀረበ

የኢትዮጵያ የሕብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት ብሔራዊ የስልጠና ማዕከል የ2014 በጀት ዓመት የሰባት ወር የስልጠና አፈጻጸም ሪፖርቱን በአዳማ ከተማ ሮቢ ሆቴል ለግምገማ እና ውይይት አቀረበ።
ዶ/ር ጌታቸው ቶሌራ የኢትዮጵያ የሕብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት ም/ዋና ዳይሬክተር የውይይት መድረኩን በከፈቱበት ወቅት እንደገለጹት የስልጠና ማዕከሉ በበጀት ዓመቱ በዕቅድ በተመሰረተ ሁኔታ ወደ ስራ በመግባቱ አጥጋቢ የሆነ ውጤት ማስመዝገብ መቻሉንና እንዲህ አይነት የውይይት መድረኮች ደግሞ የሰራናቸውን መልካም ስራዎች ብቻ የምናነሳባቸው ብቻ ሳይሆኑ ያልሰራናቸውን ስራዎች በማስቀመጥ በመወያየት በቀጣይ የምንማርባቸውን መንገዶች የሚፈጥሩ መሆናቸውን ገልጸዋል፡ ፡
አቶ መሐመድ አህመድ የስልጠና ማዕከሉ ዳይሬክተር በመድረኩ ላይ የማዕከሉን አመሰራረት፣ ተልዕኮ፣ የማኔጅመንት ሂደት፣ የሚያተኩርባቸውን የስልጠና መስኮች፣ በአፈጻጸሙ ወቅት ያጋጠሙ ችግሮችን እና የተወሰዱ የመፍትሔ እርምጃዎች እንዲሁም በአጠቃላይ የተከናወኑ ተግባራትን በጽሁፍ አቅርበዋል።
እንደ አቶ መሐመድ ገለጻ የስልጠና ማዕከሉ የኢንስቲትዩቱን አጠቃላይ የስልጠና ፕሮግራሞች ተቋማዊ በሆነ መልክ ለመምራት እንዲረዳ በ2009 ስራ የጀመረ ሲሆን ይህን ለማከናወን እስከ 2013 ዓ.ም ድረስ ተግባራዊ ማድረግ ያልተቻለ የነበረ ሲሆን አሁን ግን በዚህ በጀት ዓመት የስልጠና ፕሮግራሞችን ሙሉ በሙሉ ኃላፊነት በመውሰድ በማስተባበር ላይ ይገኛል። አሁን ባለው ሁኔታም ማዕከሉ ከሕብረተሰብ ጤና አደጋዎች ቁጥጥር ማዕከል፣ ከምርምር እና የክልል ላቦራቶሪ አቅም ግንባታ ዳይሬክቶሬቶች ጋር በጠበቀ ሁኔታ የተሳኩ ስራዎችን በመስራት ላይ ይገኛል።

በአዋሳ የተሰጠው የመስክ ኢፒዲሞሎጂ ስልጠና ተጠናቀቀ

በአዋሳ ለሕብረተሰብ ጤና አደጋ ቁጥጥር ባለሞያዎች የተሰጠው መሰረታዊ የመስክ ኢፒዲሞሎጂ ስልጠና ከሶስት ዙር ስልጠና በኋላ የተጠናቀቀ ሲሆን በዚህም 23 ባለሞያዎች ተመርቀዋል። በዝግጅቱም ወቅት ከሰልጣኞች የተለያዩ ጥያቄዎችና አስተያየቶች ተነስተው በቦታዉ ላይ የተገኙት የስራ ሃላፊዎች፤ የኢትዮጵያ የሕብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት ምክትል ዋና ዳይሬክተር አቶ አስቻለው አባይነህ እንዲሁም አቶ ማሙሽ ሁሴን እና አቶ ተስፋ ጺሆን የክልሉቹ የሕብረተሰብ ጤና አደጋዎች ቁጥጥር ማዕከል ሀላፊዎች ለተነሱት ጥቄዎች ምላሽ የሰጡ ሲሆን ከተነሱ ጥያቄዎች መካከልም ሎጅስቲክን የተመለከቱ የተለያዩ ጥያቄዎች ተነስተው አግባብ መልስ ተሰጥቶባቸዋል።
አቶ ጃፈር ከዛሊ የኢትዮጵያ የህብረተሰብ ጤና አደጋዎች ቁጥጥር ማዕከል የዝግጁነት እና የአቅም ግንባታ ዳሬክቶሬት ባለሞያ እና የስልጠናው አስተባባሪ እንደገለፁት ስልጠናው በሶስት ዙር የተሰጠ ሲሆን ከመሰረታዊ የኮምፒውተር እውቀት የበሽታ ቅኝት መረጃ እንዴት እንደሚሰባሰብ ማካተት ያለበትን እና ለሚመለከተው አካል እንዴት ሳይንሳዊ በሆነ መልኩ እንደሚቀርብ እንዲሁም ወረርሽኝ ቢከሰት ምን መደረግ አለበት መንስኤውስ ምንድነው የሚለውን በሶስት ዙር ስልጠናው ውስጥ የተካተቱ እንደነበር ጠቅለል አድርገው አስረድተዋል።

. . . በሀገራችን የጤና አትላስ

. . .ከገጽ 1 የዞረ

ጥቅም ላይ እንዲውል የማድረግ ስራ ተጠናክሮ መቀጠል እንዳለበት አስገንዝበው የጤና መረጃ በጤናዉ ዘርፍ የሚካሄዱ ምርምሮችን ለማከናወን፣ መመሪያዎችን ለማዘጋጀት፣ፖሊሲዎችን ለማዘጋጀት እና ውሳኔዎችን ለማስተላለፍ ዓይነተኛውን ሚና እንደሚጫወት አስረድተዋል።

ዶ/ር አሰፋ ደሬሳ በኢትዮጵያ የሕብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት የም/ዋና ዳይሬክተር አማካሪ በበኩላቸው የሀገራችን የጤና ዘርፍ ብዙ ምርምሮች እና ጥናቶች የሚያስፈልጉት መሆኑ በዝርዝር አስረድተው ይህንንም ለማሳካት የኢትዮጵያ የሕብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት በጤናዉ ሴክተር የተለያዩ ጥናትና ምርምር በማካሄድ ለጤና ሚኒስቴር የቴክኒክ ክንፍ እንደመሆኑ መጠን ለፖሊሲ ግብዓት ሊሆኑ የሚችሉ ሳይንሳዊ መረጃዎችን በማመንጨት ላይ ይገኛል ብለዋል።

ዶ/ር አወቀ ምስጋናው በኢትዮጵያ የሕብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት የብሔራዊ የጤና መረጃ አስተዳደር ቅመራና ትንተና ማዕከል አማካሪና በዩኒቨርሲቲ ኦፍ ዋሽንግተን ረዳት ፕሮፌሰር ባቀረቡት ገለጻ ስለ ጤና መረጃ ጠቀሜታ በጥናት የተደገፈ ገለጻ አድርገዋል። ዶ/ር አወቀ ጥናቱ ከ800 በላይ ባለሙያዎችን ያሳተፈ እና ላለፉት አምስት አመታት የተካደ እና የሀያ ዘጠኝ አመታት ዳታን የተጠቀመ መሆኑን አብራርተዋል። ጥናቱ በጤናው ዘርፍ ትልቅ እመርታና ለውጥ ለማምጣት ብሎም ያሉ መሠረታዊ ክፍተቶችን ከመፍታቱ ባሻገር የአሠራር ወጥነትን እንደሚያመጣ አስረድተዋል።

፡ በእለቱ የተመረቀው ሌላው ጥናት ደግሞ ኢትዮጵያ ባለፉት ዓመታት ውስጥ ያለፈችበትን የጤና ስርዓት በጠንካራ እና ደካማ ጎን ያሳየ ሲሆን ለፖሊሲ ግብዓት የሚሆኑ የተለያዩ የመፍትሄ አቅጣጫዎችን አስቀምጧል።

ዶ/ር ከድር ሰኢድ በዚሁ መርካቶ ላይ የጤና መረጃ አጠቃቀም እና ማጋራትን ላይ ጥናታዊ ጽሁፋቸውን ያቀረቡ ሲሆን በቀረቡት በሁለቱም ጽሁፎች ላይ ውይይቶች ተካሂደዋል። በዚህ ወርክሾፕ ላይ ከፍተኛ የስራ ሀላፊዎች፣ የዩኒቨርሲቲ ተወካዮች፣ ተመራማሪዎች፣የክልል ጤና ቢሮ ሀላፊዎች እና ሌሎች ባለድርሻ አካላት የተገኙ ሲሆን በመጨረሻም ወርክሾፑ የሚካሄድበት ሳምንት (ከመጋቢት 05 እስከ 09 2014 ዓ. ም.) (March 14-18, 2022 G.C.) የጤናመረጃ ሳምንት (Health Data Week) ተብሎ በሀገር አቀፍ ደረጃ በየዓመቱ እንዲታሰብ ከስምምነት ተደርሷል።

. . . የኮሌራ በሽታ ክትባት

. . .ከገጽ 1 የዞረ

በሶማሌ ክልል አራት ወረዳዎች በተከሰተው ወረርሽኝ 674 ሰዎች የታመሙ ሲሆን 7 ሰዎች ለህልፈተ ሕይወት በመዳረጋቸዉ ከጤና ሚኒስቴር እና ከ አጋር አካላት ጋር በመተባበር በእነዚህም ወረዳዎች 98 በመቶ የመጀመሪያ ዙር የኮሌራ ክትባት መስጠት መቻሉን ገልጸዋል።

ኢንስቲትዩቱ ከአጋሮቹ ጋር በመተባበር በአፋር እና አማራ ክልሎች ወቅታዊ እና ነባራዊ ሁኔታዎችን ከግምት ውስጥ በማስገባት የኮሌራ ወረርሽኝ ሊከሰት ይችላል ተብሎ በሚገመቱ የተመረጡ የተፈናቃይ ሰፈራ ቦታዎች (IDP sites) ከአንድ ዓመት ዕድሜ እና ከዚያ

በላይ ለሆኑ ለሁሉም ተጋላጭ የሕብረተሰብ ክፍሎች በዙር እንደሚሰጥ ጠቁመዉ ለዘመቻው አተገባበር ስኬታማነት እና የበሽታውን ስርጭት ለመቆጣጠር የሀይማኖት አባቶች፣ የጎሳ መሪዎች፣ የአካባቢ ሽማግሌዎች፣ የአካባቢው ማሕበረሰብ፣ መንግስታዊና መንግስታዊ

ያልሆኑ ተቋማት በክትባቱ ዘመቻ መሳካት ከፍተኛ አስተዋፅኦ ላደረጉ ለኢትዮጵያ የሕብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት እና አጋር ድርጅቶች ምስጋናቸውን አቅርበዋል።

በዘመቻ ማስጀመሪያው ዕለትም በጦርነቱ የተፈናቀሉ ወገኖች መጠለያ ጣቢያዎች ተጎብኝተዋል፡

.

የኢትዮጵያ የሕብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት ለቅዱስ ጳውሎስ ሚሊኒየም ሜዲካል ኮሌጅ የባዮ ሴፍቲ ካቢኔት ድጋፍ ያደረገ ሲሆን የኢንስቲትዩቱ ምክትል ዋና ዳይሬክተር አቶ አስቻለው አባይነህ በርክክቡ ወቅት ገልጸዋል።